## የታሰበው የመኖሪያ አከባቢዎች የመኪና ማቆሚያ ፍቃድ መርሐግብር (አርፒፒ) አስተዳደራዊ ፖሊሲ እና ሥነሥርዓቶች

ኦክቶበር 12/2020

ይህ ሰነድ በሚከተለው አድራሻ የሚገኘው ‹‹የየታሰበው የመኖሪያ አከባቢዎች መኪና ማቆሚያ ፍቃድ መርሐግብር (አር/ፒ/ፒ)›› ኢጋዥ ሰነድ ነው (በመኖሪያ አካባቢ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ፈቃድ (RPP) ክለሳ)። ይህ ሰነድ በአር/ፒ/ፒ መርሐግብሩ ውስጥ የታሰቡትን አበይት ለውጦች የሚሸፍን ነው፥ ይህም እንግዲህ በታሰበው መርሐግብር ውስጥ ስላሉት ስለአንዳንድ አስተዳደራዊ ፖሊሲዎች እና ሥነሥርዓቶች ዝርዝሮችን የሚያሳይ ነው። እነዚህ ዝርዝሮች በታሰበው መርሐግብር እና በነባራዊው መርሐግብር መካከል በንጽጽር በማቅረብ ለውጦቹን በማጉላት መሳ ለመሳ የቀረቡ ናቸው።

ይህም በአር/ፒ/ፒ መርሐግብሩ ውስጥ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉትን ሁሉንም አስተዳደራዊ ፖሊሲዎች እና ሥነሥርዓቶች ጠቅልሎ የያዘ ነው ማለት ግን አይደለም።

ከታሰበው መርሐግብር በተመሣሣይ ሁኔታ፥ የስታፍ አባላት የታሰበውን የአስተዳደር ፖሊሲ እና ሥነሥርዓቶች ከማህበረሰቡ በተሰሙ ነገሮች፣ በነባራዊው መርሐግብር ትንታኔ እና ከአንዳንድ የአርሊንግተን ጎዳናዎ ከተሰበሰቡ የመኪና ማቆሚያ መረጃዎች ተመርኩዘው አዘጋጅተዋል። በአር/አር/ፒ መርሐግብሩ ላይ የአርሊንግተን ነዋሪዎች ክፍፍል ይታይባቸው የነበረ ሲሆን፥ አንዳንዶቹ የሚያቃርኗቸው ምክንያቶች ደግሞ ለአስርት ዓመታት የቆዩ ናቸው። ስታፍ አባላቱም ይህንን ተግዳሮት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የመርሐግብሩን ግቦች በሚዛን እንዳስጠበቁ ለእነዚህ እልባቶችን ለመቅረጽ ጥረት አድርገዋል።

በእነዚህ ለውጦች ላይ ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገዎት፥ የስታፍ አባላት የታሰበውን መርሐግብር እንዴት አድርገው እንደደረሱበት የሚያብራራውን በተለምዶ የሚነሱ ጥያቄዎች ገጽ በዚህ አድራሻ መጎብኘት ይችላሉ።

### የታሰቡት የአር/ፒ/ፐፒ አስተዳደር ፖሊሲ እና ሥነሥርዓቶች ከነባራዊ መርሐግብሮች ጋር ሲስተያዩ

| የጉዳዩ ፈርጅ | የአሁኑ መርሐግብር | የታሰበው መርሐግብር |
|---|---|---|
| **የማመልከቻ ክንውን አዲስ ዞን** | • ማመልከቻዎች ገቢ የሚደረጉት በ100 የአድራሻ ብሎኮች ነው (ለምሣሌ በ1000 እና በ1100 19ኛ ጎዳና ኤስ መካከል ያሉ ቤተሰዎች)<br>• በርካታ ቤተሰብ ግንባታዎች ያሏቸው ቤተሰቦች በህንጻ ሆነው ሊያመለክቱ ይችላሉ፤<br>• ገደብ ለማድረግ ካስፈለገ በአንድ ብሎክ ከሚገኙ ቤተሰቦች 60% ነዋሪዎች የአርሊንግተን ካውንቲ ማመልከቻ መሙላት አለባቸው፤<br>• አርፒፒ ገደቦችን ለመጠቀም ከፈለጉ በህንጻው መኖሪያዎች ከሚገኙ 60% የሚሆኑት የህንጻው በርካታ ቤተሰቦች ማመልከቻ ያስፈልጋል፤<br>• ከመኪና ማቆሚያ ቦታዎቹ 75% በላይ የሚሆኑት የተያዙ መሆናቸውን ስታፍ አባላት በሳይት ጉብኝት ወቅት ማየት አለባቸው፤<br>• የስታፍ አባላት ካሉት ቦታዎች ከ25% በላይ የሚሆኑት ቦታዎች ‹‹ከዞኑ ውጭ መጤ›› በሆኑ ተሽከርካሪዎች የተያዙ ሆነው ማግኘት አለባቸው፤ | • ነዋሪዎች በሁለቱም የመንገዱ ዳርቻዎች ብሎኮች ማለትም በሁለት የመንገድ መጋጠሚያዎ ወየጥወይም በመንገድ መጨረሻ ላይ ያሉት መጋጠሚያዎች መካል ባሉ ቤቶች ተብለው የሚታወቁ ብሎኮች ቤተሰቦች የሚያዳርሷቸውን ምመልከቻዎች ካውንቲው ያዘጋጃል፤<br>• የቤታቸው ዓይነት ምንም ዓይነት ይሁን ምን፣ ማመልከቻ ከሚቀርብበት ብሎክ ቤተሰቦ መካከል 80% ነዋሪዎች ማመልከቻው ላይ መፈረም አለባቸው፤<br>• ካውንቲው የመኪና ማቆሚያውን አሞላ ሁኔታ ይገመግማል።፡ ምናልባት የአሞላለ ሁኔታው 85% እና ከዚያ በላይ ከሆነ ክልከላው ይፈቀዳል፤<br>• በአንድ ብሎክ ውስጥ ከሁለት ጀምሮ ወደላይ በሚወሰን ልክ የይዞታው ብዛት ጨምሮ ከተገኘ፤<br>• ነዋሪዎች ከሚከተሉት የሰዓታት ገደብ ለአንዱ ወይም ለብዙው ብቻ ሊያመለክቱ ይችላ፡<br>    ○ 8:00 ኤኤም – 5:00 ፒኤም ከሰኞ – አርብ<br>    ○ 8:00 ኤኤም – 5:00 ፒኤም ቅዳሜ/እሁድ<br>    ○ 5:00 ፒኤም – 1:00 ኤኤም ከሰኞ– አርብ<br>    ○ 5:00 ፒኤም – 1:00 ኤኤም ቅዳሜ/እሁድ |

| የጉዳዩ ፈርጅ | የአሁኑ መርሐግብር | የታሰበው መርሐግብር |
|---|---|---|
| | • የብሎኮች በመግቢያዎች የአድራሻ ምልክት ከሌላቸው ለምሣለሴ አረንጓዴ አከባቢ፣ እና መኪና ማቆሚያ የሙሣሠሉት፥ በዞን የመኪና ማቆሚያ ለማድረግ ብቁነት የላቸውም፤<br>• የጥናት መስፈርቱ ካልተሟላ፥ ለአር/ፒ/ፒ ድጋሚ ከመጠየቃቸው በፊት ነዋሪዎች ለአንድ የካላንደር ዓመት መጠበቅ አለባቸው። | • የብሎኮች በመግቢያዎች የአድራሻ ምልክት ከሌላቸው ለምሣለሴ አረንጓዴ አከባቢ፣ እና መኪና ማቆሚያ የሙሣሠሉት፥ በዞን የመኪና ማቆሚያ ለማድረግ ብቁነት የላቸውም፤<br>• የጥናት መስፈርቱ ካልተሟላ፥ ለአር/ፒ/ፒ ድጋሚ ከመጠየቃቸው በፊት ነዋሪዎች ለአንድ የካላንደር ዓመት መጠበቅ አለባቸው። |
| **የነባር ዞኖች በማመልከቻ ለመከፋፈል** | • ምናልባት አቋርጦ መጓጓዝ ችግር ሲሆን አንድን ትልቅ ዞን በንዑስ ክፍሎች ለመከፋፈል ነዋሪዎች ለካውንቲውምመልከቻ ማቅረብ ይችላሉ፤<br>• ቢያንስ በአንድ ብሎክ ከሚኖሩ መካከል 60% ቤተሰቦች ያሉበት ብሎክ አቋርጦ ለመንቀሳቀስ እንዲጠና ጥያቄ ካቀረቡ፤<br>• ስታፍ አባላት የብሎክ ወሰኑን በድንበርነት በመውሰድ 25% የሚሆኑት ከዚህ ውጭ የመሆናቸውን ጥናት ለማድረግ የ75/25 ጥናት ሊያደርጉ ይችላል፤<br>• አንድ ጊዜ የ75/25 ጥናት ተደርጎ ፍተሻው ከተሳካ፥ አዲሱ ዞን ወሰን በምን መልኩ ቢሆን ተገቢ እንደሚሆን ለመወሰን ካውንቲው ግምገማ ያደርጋል፤<br>• አዲሱ የዞን ወሰን ከተወሰነ በኋላ፥ በታሰበው ዞን ካሉት ነባራዊ የፍቃድ ባለቤቶች ቢያንስ 60% የሚሆኑት አዲስ አነስተኛ ዞን ለመፍጠር ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው፤ | • ነባር የሆነ ዞንን ከከፍተኛ የይዞታ ብዛት የተነሣ እንዲካፈል ለማድረግ ነዋሪዎች ካውንቲውን ያነጋግራሉ፤<br>• ማመልከቻ ከቀረበበት ብሎክ 80% ነዋሪዎች የሚሆኑ ቤተሰቦች ማመልከቻውን ደግፈው ፊርማቸውን ማስፈር አለባቸው፤<br>• ካውንቲውም የመኪና ማቆሚያውን ይዞታ ይመለከታል፤ ምናልባት መደበኛው የይዞታ መጠን 85% እና ከዚያ በላይ ከሆነ፥ ለአዲስ ዞኖ የሚሆኑ ወሰኖችን ካውንቲው የሚያረቅቅ ይሆናል፤<br>• ካውንቲውም በአዲሶቹ ዞኖች ውስጥ ለሚገቡት ቤተሰቦች የሚሰራጭ ማመልከቻ ካውንቲው ያዘጋጃል። ምናልባትም በታሰበው አዲስ ዞን ከሚገኙ ቤተሰቦች ቢያንስ 80% የሚሆኑት መካፈሉን ከደገፉ፥ እንግዲህ ካውንቲው አዲስ ዞን ይፈጥራል፤ |

| የጉዳዩ ፈርጅ | የአሁኑ መርሐግብር | የታሰበው መርሐግብር |
|---|---|---|
| | | ወይም<br>• አዲስ በሰዓታት እንዲገደብ ለሚቀርብ ማመልከቻ አካል እንዲሆን፥ የስታፍ አባላት የይዞታጥናቱን ውጤት ወስደው የዞኑ መጠን ለከፍተኛ ይዞታ ዳርጎት እንደሆነ ይወስናሉ። በእንደዚህ ዓይነት አጋጣሚ ካውንቲው ለአዲስ ዞኖች ወሰን ያበጃል፤<br>• በአዲሱ ዞን ውስጥ ለሚካተቱት ቤተሰቦች የሚሰራጭ ማመልከቻ ካውንቲው ያዘጋጃል። ምናልባትም በታሰበው አዲስ ዞን ከሚገኙ ቤተሰቦች ቢያንስ 80% የሚሆኑት መካፈሉን ከደገፉ፥ እንግዲህ ካውንቲው አዲስ ዞን ይፈጥራል፤ |
| **አንድን ዞን ማስወገጃ ማመልከቻ** | • አንድ ብሎክ ነዋሪዎች ምናልባት የጎዳና፣ የትራፊክ ወይም የመኪና አቋቋም አኳኋን የተቀየረ በመሆኑ ምክንያት የመኪና ማቆሚያ ፍቃድ የማያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ አንድን ዞን እንዲያስወግድ ለካውንቲው ሊያመለክቱ ይችላሉ፤<br>• በካውንቲው የቀረበው ቅጽ ከብሎኩ ነዋሪዎች ቢያንስ በ60% ያህሎቹ ጎረቤታሞ መፈረም አለበት።<br>• ምናልባት ከሚፈለገው ፊርማ 60% የሚሆነው ከተሟላ፥ ካውንቲው ከብሎኩ የመኪና ማቆሚያ ምልክቱን ያነሳል። ለብሎኩ ነዋሪዎችም የማሳሰቢያ ወረቀት የሚላክላቸው ይሆናል፤<br>• ምናልባት ነዋሪዎች የመኖሪያ አከባቢ የመኪና ማቆሚያ ፍቃዱ እንዲመለስ ከፈለጉ፥ የመጀመሪያው ማመልከቻ ከጸደቀ በኋላ | • ነዋሪዎች ከብሎካቸው ላይ ነባር የዞን ገደብ እንዲነሳላቸው ካውንቲው ማመልከቻ እንዲሰጣቸው ያነጋግራሉ፤<br>• ይህ በሚመለከታቸው ብሎኮች ከሚገኙ ቤተሰበ 80% የሚሆኑ ነዋሪዎች ማመልከቻውን ደግፈው መፈረም አለባቸው፤<br>• ምናባት የ80% ቅድመሁኔታው ከተሳካ፥ ካውንቲው ከብሎኩ የመኪና ማቆሚያ ምልክቱን ያነሳል። ለብሎኩ ነዋሪዎችም የማሳሰቢያ ወረቀት የሚላክላቸው ይሆናል፤<br>• ምናልባት ነዋሪዎች የመኖሪያ አከባቢ የመኪና ማቆሚያ ፍቃዱ እንዲመለስ ከፈለጉ፥ የመጀመሪያው ማመልከቻ ከጸደቀ በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ድጋሚ ማመልከቻቸውን ማቅረብ ይችላሉ፤ |

| የጉዳዩ ፈርጅ | የአሁኑ መርሐግብር | የታሰበው መርሐግብር |
|---|---|---|
| | በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ድጋሚ ማመልከቻቸውን ማቅረብ ይችላሉ፤ | |
| **የዞን ወሰን ማውጫ መስፈርት** | • የዞን ወሰን ማውጫ መስፈርቶች<br>○ ከ1/2 ማይል ዙሪያ ገባ ራዲየስ ያልበለጠ<br>○ አብይ ወይም አነስተኛ መተላለፊ መንገድ፣ ግዑዝ እና ተፈጥሯዊ ወሰኖች ያሉት መሆኑ፤<br>○ የሲቪክ ማህበራት ወሰኖች<br>○ የመሬት አጠቃቀም ባህርያት (የቤቶችን ዓይት አይደለም)<br>○ ትራፊክ የሚፈጠርበት ቦታ<br>○ በአከባቢው ውስጥ የሚሽከረከሩበት ልማድ፤<br>○ የመንገዶቹ መኪና የማቆም አቅም፤<br>○ የመኪና ማረፊያ እና የተመደቡ የመኪና ማቆሚያዎች መኖር<br>• በየብሎኩ በማት በአዲስ ዞኖች ወይም ለነባር ዞኖች ብሎክ ይጨመራል፤ | • የዞን ወሰን ማውጫ መስደርቶች<br>○ ቢበዛ የ1/2 ማይል ራዲያስ<br>○ አብይ ወይም አነስተኛ መተላለፊ መንገድ፣ ግዑዝ እና ተፈጥሯዊ ወሰኖች ያሉት መሆኑ፤<br>○ የሲቪክ ማህበራት ወሰኖች<br>○ የመሬት አጠቃቀም ባህርያት (የቤቶችን ዓይት አይደለም)<br>○ ትራፊክ የሚፈጠርበት ቦታ<br>○ የመንገዶቹ መኪና የማቆም አቅም፤<br>• በየብሎኩ በማት በአዲስ ዞኖች ወይም ለነባር ዞኖች ብሎክ ይጨመራል፤ |
| **በሁለት አር/አር/ፒዎች መካከል ወሰን ላይ የሚገኙ ቤተሰቦች የሚስተናገዱበት ሁኔታ** | • አንዳንድ ጎዳናዎች የሁለት ዞኖች ምልክት ይኖርባቸዋል (ምሣሌN Veitch Street ተብሎ የሚታወቀው ምልክቱ “Zone 4/6” ነው)<br>• ይዞታቸው በማዕዘን ላይ የሆኑ ቤተሰቦች የሁለት አርፒፒ ዞኖች ይለፍ ሊያገኙ ይችላሉ፤ | • ከሁለቱም ዞኖች የሚገኙተ ይሁንታዎች ከዞኑ ወሰን በአንደኛው ወገን አቅጣጫ ላለው አንደኛው ብሎክ የሚያገለግሉ ይሆናል፤<br>• ለንብረቶች ይለፍ የሚሰጠው ከአንዱ ዞን ነው፤ |

| የጉዳዩ ፈርጅ | የአሁኑ መርሐግብር | የታሰበው መርሐግብር |
|---|---|---|
| **“ከቀድሞ የሚተላለፉት”** ገደብ | አይመለከተውም | • ከቀድሞ የሚተላለፉት ብቻ የሚጠቀሙበት ወሰን እና የገደብ ሰዓታት ይኖራል |